# ግርማ የስሕተት፣ ገብሩ ደግሞ የውግዘት ሰባኪ ቢሆኑስ?

# (ክፍል ሁለት)

**(FANOWEDY SAMARA)**

**Comment on fanowedy@gmail.com**

በክፍል አንድ አል-ኢስላም የተባለ መፅሔት በያዝነው ወር (ሰኔ 2004ዓ.ም) "ተቃዋሚ ፓርቲዎች በወቅታዊ የህዝበ ሙስሊሙ አጀንዳዎች ዙሪያ ምን ይላሉ" በሚል ሶስት የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎች አመራሮች አነጋግሮ እንደነበር በክፍል አንድ አይተናል። በመፅሔቱ ከተሳተፉ የተቃዋሚ ፓርቲዎች አመራሮች መካከልም አቶ ግርማ ሰይፉ (የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ ፓርቲ ም/ሊቀመንበ) የሰጡት አስተያየትና አንድምታው በክፍል አንድ በዝርዝር ለማቅረብ ተሞክሯል።

እስቲ አሁን ደግሞ አቶ ገብሩ አስራት (የዓረና ዴሞክራሲያዊ አንድነት ሊቀመንበር፣ የመድረክ ም/ሊቀመንበር እና የውጭ ጉዳይ ኃላፊ) ከመፅሔቱ ጋር በነበራቸው ቆይታ የሰጡት አስተያየትና አንድምታው እንከታተል።

አል-ኢሰላም ጥያቄዎቸ ካቀረበላቸው የተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲ አመራሮች መካከል አቶ ገብሩ አስራት አንዱ ናቸው። አቶ ገብሩ ከመፅሔቱ የተለያዩ ጥያቄዎች ቀርበውላቸው ለጥያቄዎቹም የራሳቸው እምነትና የፓርቲያቸው አቋም አንፀባርቀዋል።

አቶ ገብሩ የቀረቡላቸው ጥያቄዎች መንግስትና ሁሉም የሃይማኖት አባቶችና መሪዎችን ለማውገዝ ተጠቅመውባቸዋል። እንደ አቶ ገብሩ አባባል ***"የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስትሩ ዶክተር ሽፈራው ተክለማርያም ባሰሟቸው ንግግሮችም ሆነ ከውጭም ባስመጧቸው የሰዎች የእርሱ ደጋፊዎች ናቸው የሚሏቸውን ጭምር እያሰማሩ ህዝበ ሙስሊሙን ከቆየው እምነት ውጭ እንዲያምን እየተደረገ ያለው እኮ በመንግስት ድጋፍ ነው"*** እያሉ መንግስትን ይኮንናሉ።

በኢትዮጵያ በርካታ ሃይማኖቶች ሕገ-መንግስቱ በሰጣቸው እኩልነትና በምእመኑ መካከል በተሰጠው ሕገ-መንግስትዊ እኩልነትና የእምነት ነፃነት መሰረት ሁሉም ሃይማኖቶች ሆኑ ባህላዊ አምልኮዎች ያልምንም ተፅእኖ የአምልኮ ስርዓታቸውን እየተገበሩና እምነቶቻቸውንም እያስተማሩ በሚገኙበት በአሁኑ ስዓት አቶ ገብሩ ደግሞ

መንግስት የአንድ ሃይማኖት ጠላት አድርገው መፈረጅን መርጠዋል። እውነታው ጠፍቶዋቸው ሳይሆን እቺም በመጠኑም ቢሆን ጊዜያዊ ፖለቲካዊ ትርፍ ይገኝባታል ከሚል የተሳሳተ መነሻቸው መሆኑን አያጠራጥርም።

በመቀጠል ደግሞ *"በየጊዜው እንደማየው ግን አማኙ ሙስሊም ራሱ በበዓል ቀን ሲሰበሰብ መሪዎቹ መንግስት ነው የሚመርቁት እንጂ ኃይማኖትን አይደለም የሚናገሩት። ስለ ዜጎች ደህንነት መልካም ስራ አይናገሩም። ክርትስተናውም ይኼው ነው የሚታየው። የሃይማኖት ድርጅቶች የመንግስትን ፖሊሲ ሲደግፉ መታየታቸው ልክ እንደ ፓርቲ ቁመና ያላቸው ነው የሚመስለው"* በማለት የሃይማኖት አባቶችን ይኮንናሉ።

ለመሆኑ የሃይማኖት አባቶችና መሪዎች መንፈሳዊ ተልዕኮ የመንግስት ፖሊሲና ስትራቴጂ መቃወም ነበር እንዴ? የሃይማኖት መሪዎቹ የመንግስትን ፖሊሲ መደገፋቸው ስህተት ከሆነ መቃወማቸው ግን ትክክል ይሆን ነበር ማለት ነውን?

የሃይማኖት አባቶቹ ከሀገሪቱ እውነታ የተነጠሉ ሳይሆኑ በሀገሪቱ ማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ ህይወት ውስጥ ያሉና ሀገሪቱ መላው ዓለም የመሰከረለት ፈጣንና ቀጣይነተ ያለው ዕድገት አካልም ጭምር በመሆናቸው ለሀገሪቱ ዕድገትና ብልፅግና ዕውቅና መስጠታቸው ስሕተት የለውም። ለምን ቢባል አባቶቹ የተከታዮቻቸው ኑሮ እንዲሻሻል ይሻሉ፣ ለተግባራዊነቱም ይተጋሉና ነው። በሌላ አነጋገር የሃይማኖት አባቶች የድህነትና የኋላቀርነት ጠባቂዎች ሳይሆኑ የምእመኑ ህይወት በዘላቂነት እንዲሻሻል ቢያስተማሩና መንግስትም ይህንን ፍላጎታቸውና ምኞታቸው ሲያሳካላቸው እውቅና ቢሰጡት ምንም ዓይነት ስሕተት የለውም።

መንግስትና ህዝብ በጋራ ሆነው እያስመዘገቡዋቸው ላሉ የልማት ድሎችና በዓለም አቀፍ ማሕበረሰብ ዘንድም ተቀባይነት ላገኘው አስገራሚው የሀገራችን ፈጣን ዕድገት ዕውቅናው ለተቃዋሚ ፓርቲዎች ለምን አልተሰጠም ከሆነ ጥያቄው ሌላ ነው። ይሄም ቢሆን ግን በምኞትና በማውገዝ ሳይሆን አማራጭ የፖሊሲ ማዕቀፍ አዘጋጅቶ ከተግባራዊ ስኬት በመነሳት የሚሰጥ እውቅና ነውና የተሻለ ስራ ማከናወንን ይጠይቃል እላለሁ። እናም የሃይማኖት አባቶችን ከማውገዝ በመቆጠብ ሀገራዊ ፋይዳ ያላቸው አማራጭ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች በማቅረብ የህዝብ ይሁንታ ለማግኘት በቁርጠኝነት መስራት ላይ ቢያተኩሩ ጠቃሚ ይሆናል እላለሁ።

ከአንድ የፖለቲካ መሪ ነኝ ብሎ የሚናገር ሰው የሚጠበቀው ተግባር የፖሊሲና የፕሮግራም አማራጭ በማቅረብ የህዝቡን ኑሮ ለማሻሻል የሚያግዙ ተግባራት ማከናወን እንጂ የሃይማኖት አባቶቹ በየብዓሉ ለሚያደርጉት ሃይማኖታዊ ንግግሮች አቃቅር እያወጡ ማውገዝን አይደለም። ለነገሩ የኛ ሀገር ተቃዋሚዎች የሚቀናቸው አማራጭ የፖሊሲ ሐሳብ አዘጋጅተው የህዝቡን ኑሮ ለመቀየር መታገል ሳይሆን ገዥው ፓርቲ በሚያከናውናቸው ፖለቲካዊ፣ ማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ ስራዎች ላይ በመንጠልጠል አቃቅር ማውጣትን ነው። መቃወም ማለት የመንግስት አፈፃፀም እየገመገሙ ከግምገማውንም ስኬቶችን እያጥላሉ አሉ ለሚሏቸው ክፍተቶች ባለ በሌለ ዓቅማቸው ማውገዝ ማለት እንደሆነ ተደርጎ እስከመታየት የደረሰበት ምክንያትም ከተቃዋሚዎች መሰረታዊ የንትርክ ባህሪ በመነሳት ነው።

አቶ ገብሩ አሰራት ኢህአዴግ እየተዳከመ መምጣቱ የሚያመላክቱ ነገሮች እንዳሉም ያትታሉ። ኢህአዴግ እየተዳከመ ወይ ደግሞ እየተጠናከረ ስለመምጣቱ ፍርዱ ለኢትዮጵያ ህዝቦች በመተው አንድ ፀሐይ የሞቀው ያደባበይ ምስጥር ብቻ በማስቀመጥ አጀንዳው ሊለፊው። በመጀመሪያ ደረጃ አቶ ገብሩ ለየትኛው ህዝብ እየተናገሩ እንዳለ ግልፅ አይደለም። ለምን ቢባል እነ አቶ ገብሩና መሰሎቻቸው ድፍን ሀገር በሚያውቀው ምርጫ 2002 ተወዳድረው በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንደተለመደው ለጭቅጭቅ የሚሆን ተወካይ እንኳን እንዳይኖራቸው በህዝቡ ተገልለው ዳር ሲይዙ ኢህአዴግ ግን በታሪኩም ታይቶ በማይታወቅ መልኩ በሁሉም የተወዳደረባቸው አካባቢዎች በፍፁም ልዕልና ተቃዋሚዎች በዝረራ አሸንፎአቸዋል። እና ይህ እውነታ ለብቻው ነጥለን በማየት እንኳን የኢህአዴግ መጠናከርን እንጂ መዳከምን የሚያሳይ እንዳልሆነ አቶ ገብሩን ጨምሮ ሁላችን የሚንገነዘበው ሐቅ ነው።

በሌላ መልኩ ደግሞ ኢህዴግ የቀየሳቸው የልማት ፕሮግራሞች ምልአተ-ህዝቡ ከዳር እስከዳር በማነቃነቅ ልማቱን እየተጧጧፈው ነው። ይህ እውነታ ከመካድ የበለጠ ክህደትም የለም። ለምን ቢባል የስኬቱ ባለቤቶች ኢህአዴግ ብቻ ሳይሆን በኢህአዴግ መርነት በሁሉ የኢትዮጵያ ህዝቦች የተገኘ ድል ነውና። በሌላ በኩል ደግሞ የዓለም አቀፉ ማሕበረሰብ ያደነቀው ስኬት እዚሁ ኢትዮጵያ ቁጭ ብሎ እውነታውን መካድ ማለት በሀገር ውስጥ እንደሌሉም ማረጋገጫ የሚሰጥ አጋጣሚ እንደሆነ ይገነዘቡታል

የሚል እምነት አለኝ። ለነገሩ እነ አቶ ገብሩ መናገር የሚጀምሩት ልማት በሚከናወንበት ወቅት ሳይሆን እዚህም እዚያም ጥቃቅን ችግሮች አሉ ብለው በሚያስቡበት ወቅት ብቻ በመሆኑ ስለልማቱ ለምን አልተናገሩም ተብሎ አይፈረድባቸውም።

ባለፉት ሁለት ተከታታይ ዓመታት በተለያዩ ክልሎች እየተከናወኑ ያሉ የተፋሰስ ልማት እንቅስቃሴዎችና በዘርፉ እየተመዘገቡ ያሉ ስኬቶች ብቻ በማየት የኢህአዴግ የልማት ፖሊሲዎች ምን ያህል በህዝቡ ልቦና ውስጥ እንደሰረፁና በህዝቡ ዘንድ ምን ያህል አመኔታ እንደተቸራቸው መገመት አያዳግትም። እና የኢህአዴግ መዳከም የት ላይ እንደሆነ የሚያሳይ ነገር አላየሁም። ለነገሩ የኢህአዴግ መዳከምም ሆነ መጠናከር የኢህዴግ ጉዳይ እንጂ የእኔ ጣጣም አይደለም። በዚህ ርእሰ-ጉዳይ ላይ ትንሽ ለማለት የፈለግኩበት ምክንያትም የአቶ ገብሩ ትንበያና በመሬት ላይ ያለው እውነታው አንገናኝም ስላሉኝ የታዘብኩትን ለማካፈል ያህል ነው።

አሁንም ቅድም ወደ ጀመርኩት የአቶ ገብሩ አባባል በድጋሚ ልመልሳችሁ። *"በየጊዜው እንደማየው ግን አማኙ ሙስሊም ራሱ በብዓል ቀን ሲሰበሰብ መሪዎቹ መንግስት ነው የሚመርቁት እንጂ ኃይማኖትን አይደለም የሚናገሩት። ስለ ዜጎች ደህንነት መልካም ስራ አይናገሩም። ክርትስትናውም ይኼው ነው የሚታየው። የሃይማኖት ድርጅቶች የመንግስትን ፖሊሲ ሲደግፉ መታየታቸው ልክ እንደ ፓርቲ ቁመና ያላቸው ነው የሚመስለው"* በማለት የሃይማኖት አባቶችን ይኮንናሉ።

እናም አቶ ገብሩ የሃይማኖት አባቶች መንግስትን እየረገሙ፣ ፖሊሲዎቹንም እየተቃወሙ በአደባባይ ካላወገዙት በቀር የአባትነት ሚናቸው እየተወጡ አይደለም እያሉን ይሆን? በእኔ እምነት አንድ የሃይማኖት አባት ሀገሪቱ ከድህነትና ከኋላቀርነት ለማላቀቅ ምልአተ-ህዝቡን ከጎኑ አሰልፎ ቀን ተሌሊት ለሚረባረብ መንግስት እነ አቶ ገብሩ እንዳሰቡት ሰበብ አስባብ እያፈላለጉ የማውገዝ መለኮታዊ ተልዕኮ ያለበት አይመስለኝም። ለወዳጅና አብሮ ለተሰለፈው ልማታዊ ሃይል ይቅርና ለጠላትም ቢሆን ብቀላን የሚያስተምር ሃይማኖት የለምና። እናም የአቶ ገብሩ ሰበካ ከሃይማኖት አባቶች የመጠቀ ሃይማኖታዊ እውቀት ላላቸው ግለሰቦች መንግስትን ለማውገዝ ይጠቅማቸው እንደሆነ የውግዘት ትምህርቱን መቀጠል ይችሉ ይሆናል።

ችግሩ ግን ሁሉም ሃይማኖቶች በመንግስት የውስጥ ጉዳይ ላይ ጣልቃ እየገቡ የተወሰኑ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምናልባትም የእነ አቶ ገብሩ ፓርቲ ለማስደሰት ብለው መንግስትን የሚያወግዙበት ሁኔታ እንፍጠር ማለት በመንግስትና በሃይመኖት መካከል የተበጀው የማያሻማ ድንበር እንመልሰው ማለት እንደሆነ ግልፅ መሆኑን ነው። እናም የሃይማኖት አባቶቹ መንግስትን ለማውገዝ ወደ አደባባይ እንዲወጡ መመኘትና መምከር ጊዜው ያለፈበት የውግዘት ሰበካ ከመሆኑም በተጨማሪ ሃይማኖታዊ ይዘትም የለውም እላለሁ።

ከምንም ነገር በላይ ደግሞ በእምነትና በሃይማኖት ሰበብ በህዝብና በመንግስት መካከል የማይታረቅ ቅራኔ ለመፍጠር ያለመ ስክነት የጎደለው የውግዘት ሰበካ መሆኑ ለማንም ግልፅ ሆኖ ሳለ አቶ ገብሩ ግን የሃይማኖት መሪዎቹ መንግስትን በመመረቃቸውና የመንግስትን ፖሊሲ በመደገፋቸው ብቻ የፖለቲካ ቁመና ያላቸው ናቸው በማለት በግላጭ ለማሸማቀቅ ሞክረዋል። እውነት ለመናገር ይህ ዓይነቱ በጥላቻ ላይ የተመሰረተ የፖለቲካ አካሄድ ተወዳድሬ ካሸነፍኩኝ የመንግስት በትረ-ስልጣን እጨብጣለሁ ለሚል የፖለቲካ ፓርቲ አመራር ነኝ ባይ ይቅርና ለማንም ሰውም ቢሆን የባከነና ሀገርን ለብጥብጥና ለሁከት የሚመራ ያልተጠና አካሄድ ነው እላለሁ።

እናም አቶ ገብሩ መንግስትና መንግስቱን እየመራ ያለው ኢህአዴግ ብቻ ሳይሆን የሃይማኖት መሪዎችና አባቶቻችን እያወገዙ የሃይማኖቶች እኩልነትና የእምነት ነፃነት የሚሉት የየትኛው ሃይማኖትና እምነት ይሆን? ምናልባትም እስካሁን ያልተሞከረው የውግዘት ሃይማኖትና የውግዘት እምነት ካልሆነ በቀር እስካሁን ባሉ የተለመዱ ሃይማኖቶችና እምነቶች የመሪዎቻቸው ተልዕኮ መንግስትን ማውገዝና የመንግት ፖሊሲን መቃወም አይመስለኝም። የሃይማኖት አባቶቻችን መንግስትን በመርገምና የመንግስት ፖሊሲዎች በመቃወም ላይ ጊዜአቸው ካባከኑማ ውግዘትና ማጥላላት እንደሃይማኖት አድርገው የተጠመቁ የእነ አቶ ገብሩ ፓርቲዎችስ ምን ይስሩ? በነገራችን ላይ አቶ ገብሩ ውግዘትን መስበክ ብቻ ሳይሆን የሃይማኖት አባቶቻችንን በግልፅ ለማሸማቀቅ እንደሞከሩት ሁሉ በግልፅ ይቅርታ መጠየቅ እንዳለባቸው ይሰማኛል። እናም ይቅርታ መጠየቅ አለባቸው ባይ ነኝ። እናንተስ ምን ትላላችሁ?